Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission



# ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን ማረጋገጥ

## በተጨባጭ ወይም በጥርጣሬ በሰዎች የጾታ ዝንባሌ ወይም በጾታ ማንነታቸው ምክንያት በእምነት ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው መከላከል

ስለ ጾታዊ ዝንባሌ እና ጾታዊ ማንነት ማውራት ለእምነት ማህበረሰቦች ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ኲየር(የተለየ ጾታዊ ማንነት ያላቸው) ትራንስ( ጾታቸውን የቀየሩ) ወይም የተለየ ጾታዊ ማንነት ያላቸው ሰዎች ባላቸው የጾታ ልዩነት ምክንያት ከእምነት ማህበረሰቦች በኩል ድጋፍ እንደሚያገኙ ካልተሰማቸው ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ።

በ2022 ቪክቶርያ ውስጥ-*Change or Suppression (Conversion) Practices Prohibition Act 2021(የመለወጥ ወይም የመጫን (የመቀየር) ልማዶች ክልከላ ህግ 2021 የሚል አዲስ ህግ ወጥቷል- ይህም የኣንድን ሰው የጾታ ዝንባሌ ወይም የጾታ ማንነት ለመለወጥ ወይም ለመጫን የሚደረጉ ሙከራዎችን የሚከለክል ነው። ኲየር፥ ትራንስ እና የተለየ የጾታ ማንነት ያላቸውን ሰዎች መቀበል ለጤናቸውና ለደህንነታቸው ኣስፈላጊ ነው።*

## የመለወጥ ወይም የመጫን ልምዶች ምንድን ናቸው?

ኣንዳንድ ጊዜ “የመለወጥ ህክምና” እየተባሉ የሚጠሩት የመለወጥ ወይም የመጫን ልምዶች የግለሰቡን ጾታዊ ዝንባሌ ወይም ጾታዊ ማንነት ለመደበቅ የሚሞክሩ እንቅስቃሴዎች ናቸው። እነዚህም ልምዶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ ፤

- ማስተማር
- የምክር ኣገልግሎት መስጠት
- የመንፈሳዊ እንክብካቤ ተግባራት
- ሌሎች ስነ-ልቦናዊ ወይም የህክምና ጣልቃ ገብነቶች።

እነዚህ ልምዶች የተመሰረቱት ስለ ኲየር ፣ ትራንስ(ጾታቸውን የቀየሩ) እና የተለየ የጾታ ማንነት ያላቸው ሰዎች ላይ የተሳሳተ ወይም የተበላሸ ነገር ኣለ ከሚል የሀሰት እና ጎጂ በሆነ ኣባባል የተመረኮዘ ነው።

እነዚህ ድርጊቶች በሰዎቹ ዘንድ ጥልቅ፥ ቀጣይነት ያለውና የረጅም ጊዜ የጤና ጉዳት የሚያደርሱ እና ራስን የማጥፋት አደጋዎችን ሊጨምሩ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ኣሉ።

## ከህግ ጋር የሚቃረኑት ተግባራት የትኞቹ ናቸው?

ከፌብርዋሪ 2022 ጀምሮ በቪክቶሪያ ውስጥ የመለወጥ ወይም የመጫን ልምዶች ታግደዋል። ህጉ የሚከተሉትን የመለወጥ ወይም የመጫን ተግባራት ናቸው በማለት ይገልጻል፤

- አንድ ሰው ላይ ያነጣጠረ ተግባር ወይም ባህርይ
- በእነሱ የጾታ ዝንባሌ ወይም የጾታ ማንነነት መሰረት ያደረገ
- በፈቃዳቸው ይሁን ከፈቃዳቸው ውጭ የጾታ ዝንባሌኣቸውን ወይም የጾታ ማንነታቸውን የመለወጥወይም የመጫን ዓላማ

Victorian Equal Opportunity & Human Rights Commission

በህጉ መሰረት፣ ጉዳት ወይም ከባድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የመለወጥ ወይም የመጫን ተግባር ወንጀል ሊሆን ይችላል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፤

- ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ የሆነ የኣካል ወይም የኣእምሮ ጤና መታወክ የሚያስከትሉ ተግባራት
- ከባድ ጉዳት የሚያስከትሉ ተግባራት- ህይወትን ኣደጋ ላይ የሚጥል ወይም ከባድ እና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ጉዳት
- ጉዳት የሚያስከትል ተግባር ለመፈጸም ሲባል ኣንድን ሰው ከቪክቶሪያ ውጭ መውሰድ
- መለወጥን ወይም የመጫን ልምድ ማስተዋወቅ

ምንም እንኳን ኣንድ ሰው የጾታ ዝንባሌው ወይም የጾታ ማንነቱን ለመለወጥ ወይም ለመጫን እርዳታ ቢጠይቅም፣ እነዚህን ድርጊቶች መፈጸም ወይም ወደሚፈጽም ሰው መላክ(ሪፈር ማድረግ) በህግ የተከለከ ነው።

### የህክምና እና የስነ ልቦና ባለሞያዎች

የጤና ባለሞያዎች ከሞያ ደረጃቸው የተጣጣመ የህክምና እና የስነ ልቦና ህክምና መስጠቱን መቀጠል ይኖርባቸዋል። ይህም ኣንድን ሰው ኣስፈላጊ ወደ ሆነ የህክምና ወይም የስነ ልቦና ህክምና እንዲያገኝ ማስተላለፍን ያካትታል። ይህንን ማክበር ያልቻሉ የጤና ባለሞያዎች ህጉን እየጣሱ እንደሆነ ይቆጠራል።

*ይህ ህግ የተደነገገው ሁሉም ሰዎች የመለወጥ ወይም የመጫን ድርጊቶችን እስካልፈጸሙ ድረስ የራሳቸውን እምነት የመከበር መብት ለማረጋገጥ የታቀደ ነው።*

## የቪክቶሪያ የእኩልነት እና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሚና ምንድነው?

ኮሚሽኑ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፤

- የመለወጥና የመጫን ተግባራት ሪፖርት መቀበልና ወደ ሌላ ድርጅት ማስተላለፍን ጨምሮ ውጤቱን የመፈለግ፥
- ከባድ፥ ስርዓታዊ ወይም ዘላቂ የሚመስሉትን የመለወጥ ወይም የመጫን ልምዶችን የመመርመር፥
- ለእምነት ተቋማት፥ ለጤና ኣገልግሎት ሰጭዎች እና ለእምነቱ ሰዎች ያተኮረ ትምህርት የመስጠት።

## የመለወጥን ወይም የመጫንን ድርጊቶችን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል፡

የመለወጥ ወይም የመጫን ድርጊቶች ካጋጠምዎት
ወይም ካዩ እርስዎ( ወይም የሚመርጡት ተወካይ) ለቪክቶሪያ የእኩልነትና የሰብዓዊ
መብቶች ኮሚሽን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

**ስልክ** 1300 292 153
**ኣስተርጓሚ** 1300 152 494
**ኢሜይል** enquiries@veohrc.vic.gov.au
**በኢንተርነት** humanrights.vic.gov.au/get-help/

### እርዳታ እና ድጋፍ

Rainbow Door (ሬይንቦ ዶር) ስፐሺያሊስት የLGBTIQ መረጃ ፥ ድጋፍና የሪፈራል ኣገልግሎት ይሰጣል

**ስልክ** 1800 729 367
**ኤስ ኤም ኤስ** 0480 017 246
**ኢሜይል** support@rainbowdoor.org.au

### ተጨማሪ ግብዓቶች

**ስለ መለወጥም ሆነ ስለ መጫን ( መቀየር) ትግበራ ክልከላ ደንብ**
humanrights.vic.gov.au/change-or-suppression-practices/about-the-csp-act/

**የኣውስትራሊያ የLGBTIQ ህብረ ባህላዊ ምክር ቤት -የህብረ ባህልና ህብረ እምነት የLGBTIQ የግለሰብም ሆነ የቡድን መረጃ ለማግኘት**
agmc.org.au